ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA
የዜጎች ጤና ለሃገር ብልፅግና!
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!

# የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ዳይሬክቶሬት የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት


**መስከረም /2015 ዓ.ም.**
**ድሬዳዋ**

# የሪፖርቱ ይዘት

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ማሻሻያ እና የከተማ የመ/ደ/ጤና ክ/አሃድ ሪፎርም
- ወረዳ ትራንስፎርሜሽን እና የማህበረሰብ ተሳትፎ
- የጤና ጣቢያ ሪፎርም እና  የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ የህክምና አሰጣጥ መመሪያ
- በጤና ጣቢያ የቀዶ ጥገና አገልግሎት
- የጤና ማበልጸግ ስትራቴጅ ፣ የማህበራዊ ንቅናቄ እና የአድቮኬሲ መመሪያ  ዝግጅት
- በት/ቤቶች፣በስራ ቦታዎች የጤና ማበልፀግ ተግባራት
- ያጋጠሙ ተግዳሮቶች
- የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA
የዜጎች ጤና ለሃገር ብልፅግና!
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!

# የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም




## <u>የጤና እክስቴንሽን ፕሮግራም ማሻሻያ (ፍኖተ ካርታ) ትግበራ</u>

በበጀት አመቱ፡ ፍኖተ-ካርታን የማስተዋወቅ ስራ በአማራ እና በአፋር ክልሎች ተሰርቷል፡፡

የ ፍኖተ-ካርታ የአተገባበር መመሪያ ተጠናቆ ለክልሎች ተሰራጭቷል፡፡

የኮምፕሬሄንሲቭ እና ቤዚክ ጤና ኬላ ስታንዳርድ ተዘጋጅቷል።

ዲዛይን ለኮምፕሬሄንሲቭ እና ቤዚክ ጤና ኬላ ተዘጋጅቶ ለክልሎች ተልኳል።

የጤና ኬላዎች ሪፎርም የአተገባበር መመሪያ ተዘጋጅቶ ለክልሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተሰርቷል፡፡

Designs of Basic HPs



Designs Comprehensive HPs





ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# የጤና ኬላ ልየታ በክልሎች ያለበት ደረጃ

| ክልል | አጠቃላይ ጤና ኬላዎች ብዛት | በአጠቃላይ የተለዩ ጤና ኬላዎች | | ቤዚክ ጤና ኬላዎች | | ኮምፕርሄሲቭ ጤና ኬላዎች | | Merged ጤና ኬላዎች | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| አፋር | **337** | **253** | **75** | 221 | **87** | 27 | **11** | 5 | **2** |
| አማራ | 3,596 | 3594 | **100** | 2,457 | **68** | 355 | **10** | 782 | **22** |
| ቤ/ጉ | **519** | **302** | **58** | 187 | **61** | 50 | **17** | 65 | **22** |
| ድሬዳዋ | 36 | 36 | **100** | 30 | **83** | 4 | **11** | 2 | **6** |
| ጋምቤላ | 174 | 171 | **98** | 123 | **72** | 17 | **10** | 31 | **18** |
| ሀረሪ | **28** | **24** | **86** | 19 | **79** | 3 | **13** | 2 | **8** |
| ኦሮሚያ | 7,169 | 6,524 | **91** | 4,582 | **70** | 795 | **12** | 1,147 | **18** |
| ሲዳማ | 560 | 560 | **100** | 389 | **69** | 67 | **12** | 104 | **19** |
| ደ/ህ/ብ/ብ/ሕ | 2,701 | 2,701 | **100** | 2,017 | **75** | 301 | **11** | 383 | **14** |
| ሶማሊ | 1,532 | 1,532 | **100** | 1,313 | **86** | 158 | **10** | 61 | **4** |
| ደ/ምዕ/ ኢት/ሕ | 856 | 856 | **100** | 632 | **74** | 93 | **11** | 131 | **15** |
| **ድምር** | **17,508** | **16,553** | **95** | **11,970** | **73** | **1,870** | **11** | **2,713** | **16** |

# በአጠቃላይ የተለዩ ጤና ኬላዎች (%)






- በአገር ደረጃ አገልግሎት በመስጠት ላይ ከሚገኙ 17,508 ጤና ኬላዎች መካከል 16,553 (95%) የሚሆኑ ጤና ኬላዎችን በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት መለየት የተቻለ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል፤

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION


**ኮምፕርሄንሲቭ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን እንዲሰጡ የተለዩ ጤና ኬላዎች በክልሎች (በ%)**




**ከጤና ጣቢያዎች/ከመ/ደ/ሆስፒታሎች ጋር የሚዋሄዱ ጤና ኬላዎች በክልሎች (በ%)**



# ኮምፕርሄሲቭ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም




- በበጀት አመቱ 21 ጤና ኬላዎች ኮምፕርሄንሲቭ የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፤
- አማራ፤ ቤ/ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ ደ/ም/ኢ/ህ እና ድሬዳዋ ክልሎች አገልግሎት ማስጀመር ያልቻሉ ክልሎች ናቸው፡፡


ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA


በአገር አቀፍ ደረጃ በሰጠማ-ጎሮ ጤና ኬላ ኮምፕርሄንሲቭ የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን የማስጀመር ስራ በይፋ ተካሂዳል



# የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ተግባራት


- ወረዳዎች ከወረዳ ትራንስፎርሜሽን አፈጻጸም አንጻር ያሉበትን ደረጃ የራስ ምዘና እንዲያካሄዱ ድጋፍና ክትትል ተደርጋል፡፡
    - በዚሁም መሰረት የራስ ምዘና ሰርተው የሚልኩ ወረዳዎችና ጤና ተቋማት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል፡፡






## Woredas reported as Model (self assessment)

- 91 model woredas(Only from 6 regions)
- 92% from 3 regions



# የ2014 በጀት ዓመት የ 2ተኛ ሩብ ዓመት የወረዳ ትራንስፎረሜሽን የማረጋገጥ ስራ

በ2ተኛው ሩብ ዓመት የራስ ምዘና ሞዴል ተብለው የተላኩ ወረዳዎች **67** ሲሆኑ በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፤

| ማብራሪያ | ብዛት |
|---|---|
| ለተከታታይ ሩብ ዓመታት ሞዴል ሆነው የቆዩ እና የተረጋገጡ ወረዳዎች ብዛት (ሞዴል ተብለው ተይዘዋል) | 21 |
| በ2014 በጀት ዓመት በ2ተኛው ሩብ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ ሞዴል ተብለው ሪፖርት የተደረጉና በዚህ ማረጋገጥ ያልተካተቱ ወረዳዎች ብዛት | 8 |
| በጸጥታ ችግርና በተሽከርካሪ እጥረት ምክንያት ያልተረጋገጡ ወረዳዎች ብዛት | 5 |
| በክልሎች በተሰራ ማረጋገጥ ሞዴል እንዳልሆኑ የተረጋገጡ ወረዳዎች ብዛት | 15 |
| በጤና ሚ/ር በተደረገው የማረጋገጥ ስራ ሞዴል ሆነው የተገኙ ወረዳዎች ብዛት | 16 |
| በጤና ሚ/ር በተደረገው ማረጋገጥ ሞዴል ያልሆኑ ወረዳዎች ብዛት | 2 |
| **ድምር** | **67** |

በአጠቃላይ በራስ ምዘና ሞዴል ተብሎ ከተለዩት 18 ወረዳዎችን ናሙና በመዉሰድ ለማረጋገጥ በተደረገዉ 16ቱ ሞዴል መሆናቸዉን ለማረጋገጥ ተችሏል

# የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ተግባራት…

- በቀጣይም የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ተግባራትን ከሁለተኛው የጤናው ሴክተር የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (HSTP-II) ጋር እንዲናበብ ተደርጎ የአተገባበር መመሪያውን እና መለኪያዎችን የመከለስ ስራ ተሰርቷል።
- መለኪያዎቹን በDHIS2 ውስጥ የማካተት ስራ እየተሰራ ይገኛል::
- ማሻሻያዎችን በማድረግ በዚሁ በጀት አመት በአዲስ ዳሽ-ቦርድ የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ተግባራት አፈጻጸም ክትትል እንደሚደረግ ይጠበቃል

# የሴቶች ልማት ቡድንን ማጠናከር

- በሴቶች ልማት ቡድን ብቃት ማጎልበቻ ስልጠና ውጤታማነት ላይ የተካሄደውን ጥናት ግኝት መሠረት የማህበረሰብ ተሳትፎ  በሚተገበርባቸው ወረዳዎች ላይ የሴቶች ልማት ቡድን አደረጃጀትን ለማጠናከር የሚረዳ መመሪያ ተዘጋጅቶ እንዲጠቀሙበት ተደርጓል፡፡
- ከዚህ ቀደም ስልጠናው ባልተጀመረባቸው ክልሎች በሶማሌ፣ ጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ለማስፋፋት በተከናወነው የዝግጁነት ዳሰሳ መሰረት  ለክልል ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል በተመረጡ 19 ወረዳዎች ለሚገኙ 458 የጤና ኤክስቴንሽንና ሱፐርቫይዘሮች የተዋረድ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በቅርቡ 7,229 ሴቶች ስልጠና መውሰድ የጀመሩ ሲሆን እነዚህም ከቤ/ጉሙዝ = 242፣ ከጋምቤላ = 918፣ ከሶማሌ = 5,034 እና ከአፋር = 1,035 ናቸው

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# የሴቶች ልማት ቡድን የብቃት ማጎልበቻ ስልጠና


| በጀት ዓመት | ስልጠና ያጠናቀቁ | የተመዘኑ | ብቁ ሆነው የተገኙ |
|---|---|---|---|
| 2011 | 158,774 | 51,243 | 47,641 |
| 2012 | 163,942 | 141,139 | 130,530 |
| 2013 | 343,832 | 225,155 | 204,000 |
| 2014 | 145,425 | 70,563 | 65,353 |
| ድምር | **811,973** | **488,100** | **447,524** |



- በበጀት ዓመቱ የሴቶች ብቃት ማጎልበቻ ስልጠና (CBT) ያጠናቀቁትን ሴቶች ቁጥር ከ666,548 ወደ 900,000 ለማድረስ እቅድ በተያዘው መሰረት 145,425 ሴቶች ስልጠና ያጠናቀቁ ሲሆን እስካሁን በተደረገው ጥረት 811,973 ሴቶች ስልጠና ወስደው አጠናቀዋል (አፈፃፀም 90%)

# የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶች ትግበራን በተመለከተ

- ከማህበረሰብ ተሳትፎና ባለቤትነት አንጻር ከዚህ የነበሩትን ስኬቶችና ማነቆዎች በመገምገም ተጨማሪ የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶች ተለይተው ከ2012 ዓ.ም. ጀምሮ በአራት ወረዳዎች የሙከራ ትግበራ ተካሂዳል፡፡
- የሙከራ ትግበራውን የጀመሩ ወረዳዎች ያሉበትን ደረጃ ለመገምገምና ከሂደቱ ለመማር በየደረጃው የሚመለከተታቸውን አካላት ያሳተፈ የአፈጻጸም ግምገማና የማነቆ ትንተና በአራቱም ወረዳዎች ተካሂዷል እንዲሁም ትግበራውን በእነዚሁ ወረዳዎች ውስጥ ወደሌሎች ጤና ጣቢያዎች የማስፋፋት ስራ ተሰርቷል፡፡
- የሙከራ ትግበራውን ከጀመሩ ወረዳዎች ለመማርና የትግበራ ሂደቱን ውጤታማነት ለመገምገም (process evaluation and documentation) በታቀደው መሰረት በበጀት አመቱ ግምገማው ተካሂዶ የግምገማው ሪፖርትም ለሚመለከታቸው አካላት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል፡፡



ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA


# አማራጭ የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶች…

- ከግምገማው የተገኙ ትምህርቶችን በመቀመርና በማካታት የሙከራ ትግበራውን በ26 ተጨማሪ ወረዳዎች ለማስፋት ከሁሉም ክልሎች ወረዳዎችን በመምረጥ ወደስራ ተገብቷል፡፡ በዚህም መሰረት፡
    - ትግበራውን መጀመር ይቻል ዘንድ የግንዛቤ ማስጨበጫና የምክክር መድረኮች ከክልል፣ ከዞን፣ ከወረዳ (የወረዳ አስተዳዳሪዎችን ጨምሮ) ለመጡ የስራ ኃላፊዎችና ከፍተኛ ባለሙያዎች ተካሂደዋል፡፡
    - ለትግበራው ከተመረጡ ወረዳዎች መካከል 24ቱ ትግበራውን ለመጀመር እንዲችሉ ከፍተኛ አሰልጣኞች ስልጠና በአራት የስልጠና ማዕከሎች የተሰጠ ሲሆን የተዋረድ ስልጠናም ተሰጥቷል፡፡
    - ከዚሁ ጎን ለጎን ክልሎች ለትግበራው በተመረጡ ወረዳዎች የጎጥ ጤና መሪዎችን ምልመላና መረጣ ማካሄድ ተችሏል ፡፡
- ሁለቱ አርብቶ አደር አከባቢዎች በመሆናቸው ነባራዊ ሁኔታውን ያገናዘበ የማህበረሰብ ተሳትፎን ለማሻሻል የማህበረሰብ ተሳትፎ ስልቶችን በማዘጋጀት የክልል ጤና ቢሮ ማናጅመንት አካላት በማቅረብ ተጨማሪ ግብዓት ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ በቀጣይ ወራትም የሙከራ ትግበራ የሚጀመር ይሆናል፡፡

# የቤተሰብ ጤና መመሪያ ህትመትና ስርጭት


- በበጀት ዓመቱ ክልሎች ለሴቶች ብቃት ማጎልበቻ ስልጠና የሚሆን **320,000** የቤተሰብ ጤና መመሪያ ተሰራጭቷል፡፡

- የቤተሰብ ጤና መመሪያን በሶማልኛ **30,000**፤ በአፋርኛ **15,000**፤ በአኟክኛ **10,000** እና በኙኤርኛ **10,000** የማሳተም ስራ በሂደት ላይ ይገኛል)፡፡






# የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አቅም ግንባታ




- በበጀት ዓመቱ በሁሉም ክልሎች በእናቶችና ህጻናት ጤና እና ጤና አጠባበቅ ትምህርትና ተግባቦት ላይ በሁሉም ክልሎች ለ29,079 ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የተቀናጀ የተሃድሶ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 26,679 ባለሙያዎች ስልጠናውን ያጠናቀቁ ሲሆን አፈጻጸሙም 92% ነው፡፡
- ለአፈጻጸሙ ምሉዕ (100%) አለመሆን እንደምክንያት የሚጠቀሱት በወሊድና ተያያዥ ምክንያቶች ስልጠና አለመውሰዳቸው፣ እንዲሁም በተወሰኑ አካባቢዎች የጸጥታ ችግር መኖሩ ነው፡፡

# የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሪፎርም ትግበራ

- የከተማ የመጀመሪያ ጤና ክብካቤ መልሶ ቅየሳ በሀገር አቀፍ ደረጃ እስከ 2013 በጀት ዓመት በ101 ከተሞች በ271 ጤና ጣቢያዎች ላይ ተግባራዊ ከሚያደርጉት ውስጥ 247 (91%) በተግባር ላይ ሲሆኑ
  - ቀሪዎቹ 24 ጤና ጣቢያዎች ምክንያቶች አገልግሎት መስጠቱን ያቋረጡ ጤና ጠቢያዎች ናቸው፡፡

- የቤተሰብ ጤና ቡድን ትግበራ በጀመሩ ጤና ጣቢያዎች 617,679 አባ/እማ ወራዎች ቤት ለቤት ተጎብኝተው ለ1,381,588 ሰዎች የተለያዩ የጤና አገልግሎቶች ተሰጥቷል፡፡ ከቤት ለቤት አገልግሎት በተጨማሪ በትምህርት ቤቶች፣ በወጣት ማዕከላትና የጎዳና ተዳዳሪዎች አገልግሎቱን አግኝተዋል፡፡

- በበጀት ዓመት የቤተሰብ ጤና ቡድን ለመጀመር ከታቀዱት 43 ጤና ጣቢያዎች መካከል 26 ጤና ጣቢያዎች ስልጠና ሰጥተው ወደተግባር ለመግባት የድርጊት መርሐ ግብር ቀርጸዋል። ቀሪዎቹ ደግሞ ወደ ተግባር ለመግባት በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# በበጀት ዓመቱ በቤተሰብ ጤና ቡድን የተሰጡ አገልግሎቶች

| ተ.ቁ | አገልግሎትየሚሰጥባቸውቦታዎች/ Implementation Area | ዕቅድ | ክንውን | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የተጎበኙ ቤቶች ብዛት (Visited Household) | 440,690 | 617,679 | 100% |
| 2 | ቤት ለቤት የጤና አገልግሎት ያገኙ ተገልጋዮች ብዛት | 102,712 | 1,381,580 | 100% |
| 3 | የተጎበኙ ት/ት ቤቶች ብዛት (Visited School) | 12,309 | 9,010 | 73% |
| 4 | በት/ት ቤት የጤና አገልግሎት ያገኙ ተገልጋዮች ብዛት | 62,350 | 244,269 | 100% |
| 5 | የተጎበኙና አገልግሎት የተሰጠባቸው ወጣት ማዕከላት ብዛት | 1,881 | 1,437 | 76% |
| 6 | በወጣት ማዕከላት የጤና አገልግሎት ያገኙ ተገልጋዮች ብዛት | 5,549 | 13,659 | 100% |
| 7 | የተጎበኙ የስራ ቦታዎች ብዛት (Visited Workplace) | 9,772 | 18,821 | 100% |
| 8 | በስራ ቦታዎች የጤና አገልግሎት ያገኙ ተገልጋዮች ብዛት | 1,502 | 133,175 | 100% |
| 9 | የተጎበኙ የጎዳና ተዳዳሪ ቦታዎች ብዛት (Visited Homeless) | 1,314 | 5,249 | 100% |
| 10 | በጎዳና ላይ የጤና አገልግሎት ያገኙ ተገልጋዮች ብዛት | 832 | 20,357 | 100% |

# አገር አቀፍ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓት ስትራቴጂክ ማዕቀፍ ዝግጅት

- ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋን ግብ ለማሳካት በምታደርገዉ ጥረት ዉስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓት ያለው ድርሻ ጉልህ ነዉ፡፡

- በአገራችን በአሁኑ ወቅት የሚታየውን ከፍተኛ ህዝብ ቁጥር እድገት፤ የበሽታ ሥርጭት፤ ፍታሀዊና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት የማግኘት ፍላጎትን ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም አዲሱን የጤና አክስቴሽን ፕሮግራም ፍኖታ ካርታን መሰረት ያደረገ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓት ስትራቴጂክ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡


- በመሆኑም በሀገራችን አሁን በተበታተነ መልክ እየተሠራ ያለውን የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓት በአንድ ስትራቴጂክ ማዕቀፍ አቀናጅቶ ለመምራት የሚያስችል አዲስ አገር አቀፍ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ሥርዓት ስትራቴጂክ ማዕቀፍ የማዘጋጀት ስራ ተጀምሮ እየተሰራ ይገኛል፡፡


- በዚህ መሠረትሥራው በአሁኑ ወቅት የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ፤ የስትራቴጂክ ማዕቀፉ ግብና ዓላማ፤ እንዲሁም የለውጥ እሳቤ በተመለከተ ተጽፎ በክቡር ሚኒስቴር ዴኤታ ለሚመራ አብይ ኮሚቴ ቀርቦ ከታየ በሃላ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ቀጣይ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# የጤና ጣቢያ ሪፎርም ተግባራት አፈጻጸም

# የ4ኛ ሩብ አመት የጤና ጣቢያ ሪፎርም አፈጻጸም (DHIS-2)




78.7% ጤና ጣቢያዎች በ4ኛው ሩብ አመት ሪፖርት አድርገዋል።

ሐረሪ፣ ድሬዳዋ፣ ሲዳማ፣ አዲስ አበባ እና አማራ ክልል ከ 90 በመቶ በላይ ሪፖርት የመላክ ምጣኔ ነበራቸው።

ዝቅተኛ የሆነ ሪፖርት የመላክ ምጣኔ በሶማሊ፣ አፋር ጋምቤላ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ተስተውሏል።

ከስታንዳርዶች አንጻር በሃገር አቀፍ ደረጃ የ4ኛ ሩብ አመት አማካይ አፈጻጸም 78% ነው።


ምዕራፍ 3፣ 6 እና 8 ላይ ዝቅተኛ አፈጻጸም ታይቷል።

በተቀሩት ምዕራፎች ከ80 በመቶ በላይ አፈጻጸም ታይቷል።

# የ2014 በጀት አመት የጤና ጣቢያ ሪፎርም አፈጻጸም (DHIS-2)

- የሃገር አቀፍ አማካይ ውጤት በየሩብ አመቱ መሻሻል አሳይቷል። በ4ኛው ሩብ አመትም በአንጻራዊነት ከፍተኛ ውጤት ተመዝግቧል።
- ከአተገባበር ስታንዳርዶች አንጻር በራስ ምዘና ውጤት መሰረት በጣም ጥሩ የሚባል አፈጻጸም በአዲስ አበባ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ታይቷል።

**Regional performances based on standards Annual performance**




| | AA | Afar | Amh | BG | DD | Gam | Har | Oro | SNNP | Sid | Som | SWE | National |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Q1 | 83.6 | 59.1 | 75.9 | 88.7 | 80.7 | 57.4 | 83.8 | 76.1 | 75.3 | 74.2 | 68.4 | 69 | 75.2 |
| Q2 | 88.7 | 59.4 | 75.5 | 92.1 | 82.6 | 59.9 | 88.4 | 77.3 | 76.5 | 74.6 | 72.9 | 72.4 | 76.5 |
| Q3 | 89.4 | 60.7 | 73.5 | 88 | 88.1 | 65.8 | 99.2 | 78.3 | 78.1 | 75.9 | 73.8 | 72 | 76.6 |
| Q4 | 88.2 | 61.5 | 78.3 | 89.1 | 79 | 67 | 85.9 | 79 | 77.6 | 75.1 | 67.3 | 77.3 | 78 |

# የጤና ጣቢያ ሪፎርም፡ የተከናወኑ ተግባራት

- በተለያየ ጊዜ በሁሉም ክልል በጤና ጣቢያ ሪፎርም አተገባበር መመሪያ ዙሪያ ድጋፋዊ ክትትሎችና የሜንተርሺፕ ስራዎች ተሰርተዋል።
- በክልል ደረጃ ለተደረጉ ድጋፋዊ ክትትሎች የሚያግዝ የበጀት ድጋፍ ተሰጥቷል።
- በሃገር አቀፍ ደረጃ የተሻለ አፈጻጸም ባስመዘገበው በአማራ ክልል በሚገኘው የጁቤ ጤና ጣቢያ ውስጥ የልምድ ልውውጥ ተካሂዷል።
- በየጊዜው በDHIS-2 መሰረት የሚመጡ ሪፖርቶችን መሰረት በማድረግ ለውሳኔ ያመች ዘንድ ግብረ መልስ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ክልል ጤና ቢሮዎች ወቅቱን ጠብቆ በየሩብ አመቱ ተልኳል።

# የተከለሰው የጤና ጣቢያ ሪፎርም አተገባበር መመሪያ

- ከነበረው 10 ምዕራፍ የያዘውን መመሪያ በማሻሻል 12 ምዕራፎች እና 131 ስታንዳርዶች ያሉት መመሪያ ተከልሶ እና በበላይ አመራሮች ጸድቆ ተጠናቋል፡፡
- በአርሶአደር እና አርብቶአደር አካባቢዎች በሚገኙ ጤና ጣቢያዎች የሙከራ ትግበራ ተካሂዷል፡፡
- 50 በመቶ ጤና ጣቢያዎችን ታሳቢ በማድረግ የበጀት ድጋፍ ለሁሉም ክልሎች ተልኳል።
- ከ997 (26%) ጤና ጣቢያዎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች የተዋረድ ስልጠና ተሰጥቷል
- DHIS-2 ሙሉ በሙሉ ተካቶ ተግባራዊ እስከሚሆን አፈጻጸሙን መከታተያ ዳሽ ዳሽቦርድ ተዘጋጅቶ ሪፖርቶች በመሰብሰብ ላይ ይገኛሉ፡፡
- በ2015 በጀት አመት በ100% ጤና ጣቢያዎች ስልጠናውን ተደራሽ ለማድረግ ታቅዷል።

# የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ የህክምና አሰጣጥ መመሪያ

- እስከ 2013 ዓ.ም. 2053 ጤና ጣቢያዎችን በማሰልጠን ወደስራ እንዲገቡ ተደርጓል
- በ2014 ዓም ለተጨማሪ 1338 ጤና ጣቢያዎች የተዋረድ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን ይህም በሃገር ዓቀፍ ደረጃ ያለውን የስልጠና ሽፋን ወደ 3,391 (90 በመቶ) አድርሶታል
- በዋናነት የ ስታንዳርዶችና ማረጋገጫዎች ክለሳ እንዲሁም በድጋፋዊ ክትትል ወቅት የተገኙና ከዚህ በፊት ግልጽ ያልነበሩ ጉዳዮችን የማጥራት ስራ ተካሂዶ የመመሪያው ክለሳ ተጠናቆናታትሞ ለሁሉም ክልሎች ተሰራጭቷል።
- በ2015 በጀት አመት በ100% ጤና ጣቢያዎች ለማስፋት ታቅዷል።

# የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ የህክምና አሰጣጥ መመሪያ የቀጠለ...

- ከተከለሰው የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብክቤ ህክምና አሰጣጥ መመሪያ ጋር ለማጣጣም የአንድሮይድ መተግበሪያውን የመከለስ ስራ ተሰርቷል

- በኮምፒዩተር፣ በአንድሮይድና አፕል ስልኮች እንዲሁም በታብሌቶች መስራት የሚችል web-based app እየተሰራ ሲሆን በአሁኑ ሰዓትም የሙከራ ትግበራ ማካሄድ የሚያስችል ሶፍትዌር በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

- የስልጠና ሂደቱንም ከማዘመን እና ለስልጠና የሚወጣ ወጪን ከመቀነስ አንጻር የ e-learning platform ከዚሁ አጋር ድርጅት ጋር በትብብር እየተሰራ ሲሆን የስልጠና ማሳለጫዉ ሲስተም ተጠናቋል።

# የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሀድ ጥምረት ለጥራት (EPAQ)

- የአፈፃፀም ክፍተቶችን መነሻ በማድረግ መመሪያዉን መከለስ ተችሏል
- በአፈፃፀም መስፈርቱ መሰረት 32 ጤና ጣቢያዎች እና 30 ወረዳዎች በክልሎች ተገምግመዉ የተሻለ አፈፃፀም ካላቸዉ ዉስጥ በ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በአማራ፣ በድሬዳዋ፣ በአዲስ አበባ፣ በሀረሪና በሶማሊ ክልሎች 8 ወረዳዎችና 10 ጤና ጣቢያዎችን ማየት ተችሏል።
- በበጀት እጥረት ምክነያት የእዉቅና ፕሮግራም ማካሄድ አልተቻለም።

# የጤና ጣቢያዎች የኢንፌክሽን መከላከልና መቆጣጠር (IPC)

- የጤና ጣቢያዎችን የኢንፌክሽን መከላከልና መቆጣጠር ተግባር ለማገዝ የCASH/IPC የአተገባበር መመሪያ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በማዘጋጀት ወደ ስራ ተገብቷል።
- በተጨማሪም የማኑዋል ለጤና ጣቢያዎች በሚሆን መልኩ ተከልሷል።
- ለሁሉም ክልሎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡
- በ150 ጤና ጣቢያዎች የመሰረታዊ IPC ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡
- በ2015 በጀት አመት ወደሌሎች ጤና ጣቢያዎች የማስፋት ስራ ለመስራት ታቅዷል።

# የጤና ጣቢያዎች የመልካም አስተዳደር ኢንዴክስ (Good Gov’ce Index in HCs)

- ከሁሉም ክልሎች ተወካዮች ጋር በመተባበር የአተገባበር ማኑዋል ተዘጋጅቷል
- 10 ጤና ጣቢያዎች ለሙከራ በመምረጥ የሙከራ ትግበራ ተከናዉኗል
- ከሙከራ ትግበራውም የተገኙ ግብዓቶችንም በማንዋሉ ላይ ማካተት ተችሏል፡፡
- በተመረጡት ጤና  ጣቢያዎች በአካል በመውረድ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል።
- በ2015 በጀት አመት ወደሌሎች ጤና ጣቢያዎች የማስፋት ስራ ለመስራት ታቅዷል።

# በጤና ጣቢያ የቀዶ ጥገና አገልግሎትን ማስፋፋት

- በ2014 በጀት አመት በዕቅድ ተይዘው ከነበሩት 100 ጤና ጣቢያዎች ውስጥ በድምሩ 13 ጤና ጣቢያዎች ማለትም በኦሮሚያ 11 እና በሐረሪ 1 እና በድሬዳዋ 1 ጤና ጣቢያ የቀዶ ጥገና ህክምና አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል።
- ጤና ጣቢያዎችን ስራ ለማስጀመር እንዲቻል ኮሚቴ ተዋቅሮ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራ ይገኛል።
- ከሰው ሃብት ልማት ዳይሬክቶሬት ጋር በመሆን የሰው ሃይል እጥረትን ለመቅረፍ የካሪኩለም ዝግጅት እየተሰራ ይገኛል።

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# የጤና ማበልጸግና የጤና አጠባበቅ ትምህርትን ዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸምን በተመለከተ

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# አገር አቀፍ የጤና ማበልጸግ ስትራቴጅክ እቅድ እና የአድቮኬሲ እና የማህበራዊ ንቅናቄ መመሪያ ማጠናቀቅ እና ማስተዋወቅ

- የጤና ማበልጸግ ስትራቴጅክ እቅድ በማዘጋጀት በማኔጅመንት ኮሚቴው ማፀደቅ ተችሏል፡፡
- 40 ለሚሆኑ የኢትዮጵያ የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ማበልፀግ ማህበር አባላት በበይነ-መረብ(virtual meeting) አማካኝነት እና 28 ለሚሆኑ በፕሮገራም ዘርፍ ለተውጣጡ ባለሙያዎች የማስተዋዎቅ ስራ ተሰርቷል፡፡
- የፀደቀውን ስትራቴጅ ለአጋር አካላት፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ ክልል ጤና ቢሮዎች እና ሴክተር መስሪያ ቤቶች በአገር አቀፍ ደረጃ ለማስተዋወቅ የማስጀመሪያ ዓውደ-ጥናት ለማካሄድ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተጀምሯል
- አገር አቀፍ የአድቮኬሲ እና የማህበራዊ ንቅናቄ መመሪያ የተለያዩ አጋር አካላትን በማሳተፍ ለማዘጋጀት ተችሏል

# በጤና ተቋም የጤና አጠባበቅ ትምህርትን ማጠናከር

- የጤና ተቋም ጤና አጠባበቅ ትምህርት አተገባበር መመሪያ ላይ ለጤና ተቋማት የተዋረድ ስልጠና ለመስጠት ለክልሎች የበጀት ድጋፍ ተደርጓል፣


- 12,000 ኮፒ የጤና ተቋማት የጤና አጠባበቅ ትምህርት አተገባበር ማኑዋል የህትመት ስራ ተጠናቆ ለክልሎች ተሰራጭቷል፣

- በጤና ተቋማት የሚሰጡ የጤና ማበልጸግና የጤና አጠባበቅ ትምህርት አገልግሎቶችን በተመለከተ ወጥ የሆነ የሪፖርት ፎርማት እተዘጋጀ ይገኛል፡፡

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# በጤና ተቋም የጤና አጠባበቅ ትምህርትን ማጠናከር…


- በጤና ተቋም የጤና አጠባበቅ ትምህርት አተገባበር መመሪያ ላይ በድምሩ ለ1,170 ጤና ተቋማት የተዋረደ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡



ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# በጤና ተቋም የጤና አጠባበቅ ትምህርትን ማጠናከር...

- የተዋረድ ስለጠናውን የወሰዱ 1381 የሚሆኑ ጤና ተቋማት በጤና ተቋም የጤና አጠባበቅ ትምህርት አሰጣጥ መመሪያ ላይ ትግበራ ጀምረዋል፡፡



ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# በት/ቤቶች የተቀናጀ የጤና ማበልጸግ ተግባራትን ማጠናከር

- ሁሉን አቀፍ የትምህርት ቤት ጤና ፕሮግራም ትግበራን ለማህበረሰብ ተሳትፎ ትግበራ በተመረጡ ወረዳዎች ላይ የሚገኙ ት/ቤቶችን ክልሎች ለይተው እንዲልኩ የመለያ መስፈርት የተላከ ሲሆን ሁሉም ክልሎች መስፈርቱ መሰረት ት/ቤቶችን ለይተው እንዲልኩ ተደርጎ ፤የተላኩ ት/ቤቶችንም የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡

- ለትግበራ ማጠናከሪያ የሚውል የበጀት ድጋፍም ተደርጓል፡፡ የት/ቤት ጤና ፕሮግራም ትግበራ ልምዶችን ለመለዋወጥ እና በማረጋገጥ ስራው የተለዩ ክፍተቶች እና መልካም ተሞክሮዎች ላይ ከክልል ጤና ቢሮዎች እና ከፌደራል እንዲሁም ከክልል ትምህርት ቢሮ ለተውጣጡ 40 ለሚሆኑ ባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተሰርቷል፡፡

- በተጨማሪም ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ አማራ፣ ሶማሌ፣ ሲዳማ፣ ጋምቤላ፣ እና ቤንሻንጉል የማህበረሰብ ተሳትፎ ተግባራዊ በሚደረግባቸው ወረዳዎች ለሚገኙ ሁሉም ት/ቤቶች በሚሰሩ ስራዎች ዙሪያ ከክልል ት/ቢሮ ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት ስልጠና ተሰጥቷል

# በስራ ቦታዎች የስራ ቦታ የጤና ማበልፀግ ተግባራትን ማጠናከር

- በፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ የስራ ቦታ የጤና ማበልፀግ ተግባራትን ለማከናወን የልየታ ስራ የተሰራ ሲሆን በተለዩት 12 ፋብሪካዎች ዉስጥ ለሚሰሩ 24 ለሚሆኑ የጤና ባለሙያዎች በሚተገበሩ የጤና ማበልፀግ ስራዎች ዙሪያ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- ከፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን አጠቃላይ ሆስፒታል ጋር በጋራ በመሆን በማረሚያ ቤቶች የጤና ማበልጸግ ተግባራትን ለማጠናከር ከዚህ በፊት ስልጠና በተሰጣቸዉ በሁሉም ፌደራል ማረሚያ ቤቶች ድጋፋዊ ክትትል የተደረገ ሲሆን የጤና ማበልጸግ ስራዎችን ለመተግበር የሚያስችላቸዉ ሰነድእንዲደርሳቸዉ ተደርጓል፡፡

# የድንገተኛ የጤና ስጋት ተግባቦት

- ከEPHI ጋር በመቀናጀት ለድንገተኛ የጤና ስጋቶች ተጋላጭ በሆኑ ሶስት ክልሎች (በአፋር፤ አማራ እና ኦሮሚያ) IDP እና refugee ካምፖች ላይ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡

- በዳሰሳው ጥናት ውጤት መሰረት የድንገተኛ የጤና ስጋት ተግባቦትና እና የማህበረሰብ ተሳትፎ (Risk communication and community engagement) አቅምን ለማጠናከር ለ45 ከክልሎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች በጤና ስጋት ተግባቦት እና በማህበረሰብ ተሳትፎ ዙሪያ የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ የተፈናቃይ መጠለያ ካምፖች (IDP and refugee camp) ለተውጣጡ ጤና ባለሙዎችና የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች የተዋረድ ስልጠና እንዲሰጥ የበጀት እና የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- በዚህም መሰረት ኦሮሚያ ለ156 እና አማራ ለ63 ከዞን፣ ከወረዳ እና ተፈናቃይ ካምፖች ለተውጣጡ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

# ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

- ለጤና ኤክስቴንሽን ማሻሻያ አፈጻጸም ረገድ የአመራር ትኩረት አናሳ መሆን
- ከክልሎች ሪፖርት በወቅቱ አለመላክ
- የቅንጅታዊ አሰራር ክፍተት
- የጸጥታ ችግር
- የግዢና ህትመቶች በወቅቱ አለመድረስ
- የበጀት እጥረት እና በወቅቱ አለማወራረድ
- የSDG በጀት መዘግየት (በጀት በወቅቱ አለመለቀቅ)፣ የተመደበውም በጣም ውስን መሆን፣ እና በወቅቱ አለማወራረድ

# የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- የአድቮኬሲ ሥራዎችን ተበገኙ አጋጣሚዎች ሁሉ ለመሥራትና የአመራሩን ትኩረት አእንድያገኝ ጥረት ተደረጓል
- በበየነመረብና አአካል በመገኘት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ችግሮችን ለመቅረፍ ተሞክሯል
- ከጤናዉ ሰክተር አጋሮችና ከሚመለከታቸዉ ሰክሮች ጋር በመቀናጀት ለመፍታት መሞከር
- ከህትመት፣ ከግዢና ከበጀት ጋር በሚያያዙ ጉዳዮች ላይ ከአመራሮች ጋር ተደጋጋሚ ዉይይቶች በማድረገረ ለመፍታት ጥረት ተደርጓል

MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA



# Thank you